CLADDING SAFETY Victoria

# የእሳት አደጋን ለመከላከል ሁሉም ሰው የሚጫወተው ሚና አለው

እርስዎ በሚኖሩበት ህንጻ ላይ በውጭ በኩል ተቀጣጣይ የሆነ መሸፈኛ መገኘቱ የሚኖሩበት ህንጻ ለመኖሩያ ተገቢ አይሆንም ማለት አይደለም። ይሁንና አንድ ጊዜ እሳት ከተነሳ ይህ ተቀጣጣይ የሆነው መሸፈኛ እሳቱን ለማዛመት ሊያግዝ ይችላል።

የእሳት አደጋን ለመቀነስ እና እራስዎን፣ ጎረቤቶችዎን እና የራስዎን ቤተሰብ ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ እርስዎ የግድ ሊከተሉዋቸው የሚገቡ ቀለል ነገሮች አሉ።



ባልኮኒዎች (በረንዳዎች) ላይ ሲጋራ አያጭሱ



ባልኮኒዎች (በረንዳዎች) ላይ ባርብኪው አያድርጉ



ባልኮኒዎች (በረንዳዎች) ላይ የጋዝ በርሜሎችን አያስቀምጡ



የጭስ ማስጠንቀቂያዎች (ስሞክ አላርሞች) እንዳልተሸፈኑ ወይንም እንዳልተነቀሉ እና በየወሩ እንደተሞከሩ ያረጋግጡ። ባለ ዘጠኝ ቮልት ባትሪዎችን በየአመቱ ይቀይሩ። በሊትየም ባትሪ ለአስር አመት ወደሚሰሩ የጭስ ማስጠንቀቂያዎች (ስሞክ አላርሞች) መቀየሩን ያስቡበት።



ባልኮኒዎችን (በረንዳዎችን)፣ መተላለፊያ መንገዶችን (ኮሪደሮችን) እና የአደጋ ጊዜ መውጫዎችን ከተከመረ እቃ እና ከቆሻሻ ነጻ ያድርጓቸው። በአደጋ ጊዜ የመውጫ እቅድ እንዳለዎት ያረጋግጡ።



ልብሶችን እና ሌሎች ቁሳቁሶችን ከአየር ማቀዝቀዣው ቢያንስ ቢያንስ አንድ ሜትር አርቅው ያስቀምጡዋቸው።